የወ/መ/ቁጥር 157929

የልደታ ምድብ 1 ኛ ወንጀል ችሎት

ሰኔ 14 ቀን 2002 ዓ.ም

ዳኛ ውበቱ አሰፋ

ከሳሽ፡ የፌደራል ዐ/ሕግ - አቶ መሳይ ተድላ ቀረበ

ተከሳሽ፡ አቶ አለምሰገድ ሲሳይ ወ/ማርያም - ከማረሚያ ቤት ቀረበ

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰጠ።

ፍርድ

ዐ/ሕግ ጥቅምት 13 ቀን 2002 ዓ.ም በተፃፈ የክስ አቤቱታ በአንደኛው ክስ ተከሳሽ በ1996 ዓ.ም የወጣውን የወንጀል ሕግ አንቀፅ 555(ለ) ላይ የተደነገገውን በመተላለፍ በሌላ ሰው ላይ የዘወትር ጠንቅ በሚያተርፍ ሁኔታ ሐምሌ 06 ቀን 2001 ዓ.ም በግምት ከምሽቱ 1፡30 ሰዓት ሲሆን በንፋስ ስልክ ላፍቶ ክፍለ ከተማ ቀበሌ 02 ክልል ልዩ ቦታው መካኒሳ ቆሬ ሰላም የነርሶች ኮሌጅ ፊት ለፊት ካለው አካባቢ የግል ተበዳይ አቶ ይድዲያ ስለሺን ድንጋይ ወርውሮ የፊት ለፊት ጥርሱን በመምታት በመስበሩ በፈፀመው ከባድ የአካል ጉዳት ማድረስ ወንጀል ተከሷል፡ በሁለተኛው ክስ ደግሞ በ1996 ዓ.ም የወጣውን የወንጀል ሕግ አንቀጽ 556(2)(ሀ) ላይ የተደነገገውን በመተላለፍ በሌላሰው አካል ላይ ጉዳት ለማድረስ በማሰብ በአንደኛው ክስ በተመለከተው ጊዜና ቦታ የግል ተበዳይ 1 ኛ) አቶ ይድዲያ ስለሺ ላይ አንድ ጊዜ ድንጋይ በመወርወር ግንባሩን እና አፍንጫው ላይ በመምታት የመሰንጠቅ እና ደም እንዲፈሰው ያደረገ ሲሆን እንዲሁም 2 ኛ) አቶ ዘመኑ ሐሰን ላይ አንድ ጊዜ ድንጋይ በመወርወር ግንባሩ ላይ በመምታት እንዲቆስል እና ደም እንዲፈሰው በማድረጉ በፈፀመው ቀላል የአካል ጉዳት ማድረስ ወንጀል ተከሷል በማለት ያቀረበ ሲሆን የዐ/ሕግ የክስ አቤቱታ ለተከሳሽ ደርሶትና ተነቦለት ከተረዳው በኋላ ክሱን ሳይቃወም፤ ድርጊቱን አልፈፀምኩም፤ ጥፋተኛም አይደለሁም ብሎ ክዶ በመከራከሩ ዐ/ሕግ የግል ተበዳዮችን ጨምሮ አራት ምስክሮችንና በተበዳዮች ላይ የደረሰውን ጉዳት የሚገልፅ የሐኪም ማስረጃ አቅርቦ ያሰማ ሲሆን ፍ/ቤቱም ማስረጃዎችን ከሰማ በኋላ በግል ተበዳዮች ላይ በተከሳሽ ድንጋይ መወርወር ምክንያት ጉዳት የደረሰባቸው መሆኑ የተረጋገጠ ሲሆን በአንደኛው የግል ተበዳይ አቶ ይድዲያ ስለሺ ላይ የደረሰው ጉዳትን በተመለከተ ማስረጃዎች በወንጀል ሕግ አንቀፅ 555(ለ) ላይ የተመለከተውን የሌላ ሰውን አካል ወይም አስፈላጊ ከሆኑት ብልቶቹ ወይም ሕዋሳቶቹ አንዱን ያጎደለ፤ እንዳያገለግሉት ያደረገ ወይም በሚያሰቅቅና ጉልህ ሆኖ በሚታይ ሁኔታ መልኩን ያበላሸ እንደሆነ

የሚል ስለሆነ የግል ተበዳዩን ጥርስ ፍ/ቤቱ ሲመለከተው በጠቅላላ የጎደለ ወይም እንዳያገለግል ስለመሆኑ የሚያመለክት ነገር አልተገኘም። በመሆኑም ተከሳሽ በሁለቱ የግል ተበዳዮች ላይ ላደረሰው ጉዳት በወንጀል ሕግ አንቀፅ 556(2)(ሀ) ስር እንዲከላከል በወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ሥነ ሥርዓት ቁጥር 142(1) መሰረት ታዟል። ይሁን እንጅ ተከሳሽ የመከላከያ ማስረጃ ለማቅረብ እንደማይችል ለፍ/ቤቱ የገለፀ ስለሆነ፤ ይህ ደግሞ የቀረበበትን ክስና ማስረጃ ለማስተባበል የማይችል መሆኑን ስለሆነ ተከሳሽ በሁለቱ ተበዳዮች ላይ ላደረሰው ጉዳትና በዚሁም ምክንያት እንዲከላከል በተባለበት በወንጀል ሕግ አንቀፅ 556(2)(ሀ) ስር ጥፋተኛ ነው በማለት በወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ሥነ ሥርዓት ቁጥር 149(1) መሰረት ውሳኔ ተሰጥቷል።

<u>የቅጣት አስተያየት</u>

<u>ዐ/ሕግ</u>፡ ተከሳሽ ድርጊቱን በሁለት ተበዳዮች ላይ ስለፈፀመና ይህ ደግሞ በወንጀል ሕግ አንቀፅ 60(3) መሰረት ተደራራቢ ጥፋት ስለሆነ በወንጀል ሕግ አንቀፅ 85 መሰረት ቅጣቱ ከብዶ በቅጣት መመሪያው መሰረት እንዲወሰን በማለት አመለከተ።

<u>ተከሳሽ</u>፡ ዕድሜዬ 34 ዓመት ነው፤ ትዳር የለኝም፤ በአሁኑ ወቅት ሁለተኛ ዲግሪዬን እየተማርኩ ነው፤ አንደ የአስር ዓመት ልጅ አለኝ፤ የሚኖረው ኮምቦልቻ ከተማ ከእናቱ ቤተሰቦች ጋር ነው፤ በየወሩ ገንዘብ ለእሱ እቆርጣለሁ፤ የወር ገቢዬ ብር 4401 ነው፤ ስለሆነም ፍ/ቤቱ ቅጣቱን በገደብ እንዲያደርግልኝ በማለት አመለከተ።

ፍ/ቤቱም መዝገቡን መርምሮ የሚከተለው የቅጣት ውሳኔ ወስኗል።

<u>ውሳኔ</u>

በወንጀል አድራጊ ላይ የሚወሰነው ቅጣት ወንጀል ሕጉን ግብና ዓላማ ሊያሳካ እንደሚገባ የታመነ ነው። በዚህም መሰረት የወንጀል ሕግ ዓላማ ለጠቅላላው ጥቅም ሲባል የአገሪቱን መንግስት፤ የነዋሪዎቿን ሰላም፤ ደህንነት፤ ሥርዓት፤ መብትና ጥቅም መጠበቅና ማረጋገጥ ነው።

የወንጀል ሕግ ግብ ደግሞ በዋናነት ስለወንጀሎችና ስለቅጣታቸው በቅድሚያ ማስጠንቀቂያ በመስጠት ወንጀል እንዳይፈፀም መከላከል ሲሆን፤ ሕጉን ተላልፈው ወንጀል የሚፈፅሙትን ደግሞ ተቀጥተው ሌሎች ወንጀል እንዳይፈፅሙ፤ እንዲቆጠቡና ለሌሎች ማስተማሪያ እንዲሆኑ ወይም እንዲታረሙ በማድረግ ወይም ተጨማሪ ወንጀሎች እንዳይፈፀሙ እርምጃዎች እንዲወሰድባቸው ማድረግ ስለመሆኑ በ1996 ዓ.ም ከወጣው የኢ.ፌ.ዲ.ሪ.የወንጀል ሕግ አንቀፅ 1 ድንጋጌ ለመገንዘብ ይቻላል።

የወንጀል ሕጉን ግብና ዓላማ ለማሳካት ፍ/ቤቱ በወንጀለኛው ላይ የሚወስነው ቅጣት በአንድ በኩል ወጥነትን፤ ተመዛዛኝነትን እና ፍትሀዊነትን ለማረጋገጥ በሌላ በኩል ደግሞ የወንጀል አድራጊውን ግላዊ ባህሪና የወንጀል አፈፃፀም ኩበደት መዝኖ ቅጣት ለመወሰን እንዲያስችል ታስቦ የወጣውን የፌደራል ጠቅላይ ፍ/ቤት የወንጀል ቅጣት አወሳሰን መመሪያ ቁጥር 1/2002 እና የወንጀል ሕጉን ድንጋጌዎች መሰረት ተደርጎ የሚከተለው ቅጣት ተወስኗል።

ጥፋተኛ የተባለበት በ1996 ዓ.ም የወጣው የወንጀል ሕግ አንቀፅ 556(2) (ሀ) ደረጃ የወጣለት ወንጀል በመሆኑ በቅጣት አወሳሰን መመሪያው ክፍል ሦስት ንዑስ ክፍል አንድ እና አባሪ 3 መሰረት ደረጃውን ለመወሰን በእያንዳንዳቸው የግል ተበዳዮች ላይ የደረሰውን ጉዳት መሰረት በማድረግ በግል ተበዳይ አቶ ይድዲያ ስለሺ ላይ የደረሰው ጉዳት የወንጀሉ ደረጃ 2 ሲሆን ተጓዳኝ እርከኑ 5 ነው። የእርከን 5 ፍቅድ ስልጣን ከ6 ወር እስከ 9 ወር ሲሆን ፍ/ቤቱ ሰባት ወር ከሃያ ቀንን መነሻ ቅጣት በማድረግ ወስኗል። በግል ተበዳይ ዶ/ር ዘመኑ ሐሰን ላይ የደረሰውን ጉዳት በተመለከተም የወንጀሉ ደረጃ 2 ሲሆን ተጓዳኝ እርከኑም 5 ሆኖ የፍ/ቤቱ ፍቅድ ስልጣን ደግሞ ከ6 ወር እስከ 9 ወር ስለሆነ ፍ/ቤቱ ሰባት ወር ከአስራ አምስት ቀንን መነሻ ቅጣት በማድረግ ወስናል። ተከሳሽ ተደራራቢ ጥፋት መፈፀሙ ከላይ የተመለከተ ስለሆነና ቅጣቱም የሚወሰነው በወንጀል ሕግ አንቀፅ 85 እና ከአንቀፅ 184-188 ባለው መሰረት ስለሆነ፤ አሁን የተያዘው ጉዳይ የሚታየው በወንጀል ሕግ አንቀፅ 184(1)(ለ) መሰረት ሆኖ ለእያንዳንዱ ቅጣት የተወሰነው ተደምሮ የሚወሰን ስለሆነ የሁለቱ ቅጣቶች ድምር ደግሞ አስራ አምስት ወራት ከአምስት ቀን ወይም አንድ ዓመት ከሦስት ወር ከአምስት ቀን ይሆናል። ከዚህ በመቀጠል ደግሞ ይህ የሁለቱ ድምር የሆነው ቅጣት በመመሪያው አንቀፅ 15(1)(ሀ) መሰረት የት እርከን ላይ እንደሚወድቅ መለየት ያለበት ሲሆን ይህም በአባሪ 1 መሰረት እርከን 8 ይሆናል። የእርከን 8 ፍቅድ ስልጣን ደግሞ ከአንድ ዓመት ከሁለት ወር እስከ አንድ ዓመት ከስድስት ወር ነው።

ዐ/ሕግ በወንጀል ሕግ አንቀፅ 84 መሰረት ጠቅላላ የቅጣት ማክበጃ እንዳለው ተጠይቆ ያላቀረበ ስለሆነ ፍ/ቤቱ በዚህ ረገድ ቅጣቱን አላከበደውም። በሌላ በኩል ተከሳሽ የቅጣት አስተያየት እንዲያቀርብ ተጠይቆ በወንጀል ሕግ አንቀፅ 82 ወይም/እና 86 መሰረት በማስረጃ ተደግፎ የቀረበ የቅጣት ማቅለያ ያላቀረበ ስለሆነ ፍ/ቤቱ ቅጣቱን አላቀለለውም።

በመሆኑም ፍ/ቤቱ ከላይ በተገለፀው እርከን 8 ላይ ያለውን ፍቅድ ስልጣን መሰረት አድርጎ የተከሳሽን የትምህርት ደረጃና የኑሮ ሁኔታ ከግንዛቤ በማስገባት ተከሳሹን ያርመዋል ወደፊትም ያስተምረዋል ብሎ በታመነበት በአንድ ዓመት ከሦስት ወር ቀላል እስራት እንዲቀጣ ተወስኗል።

<u>ትዕዛዝ</u>

1 ኛ. የአዲስ አበባ ማረሚያ ቤት ተከሳሹ ማረሚያ ቤት ከገባበት ጊዜ ጀምሮ በማሰብ ቅጣቱን እንዲያስፈፅም ታዟል።

2 ኛ. የቅጣት ውሳኔው ዛሬ ሰኔ 17 ቀን 2002 ዓ.ም ተነበበ።

2 ኛ. የይግባኝ መብት እንዳለ በችሎት ተነገረ።

3 ኛ. በዚህ መዝገብ የተገባ የዋስትና ግዴታ ቀሪ ሆኗል።

4 ኛ. መዝገቡ ተዘጋ ወደ መ/ቤት ይመለስ።